# <u>የእርኩስ መንፈስ አርካሽ</u>

ላፈዘዘን ሰይጣን ለሚያደነዝዘን፣

ውሸት በማራባት፣ለሆድ ባደሩለት ክፋፍሎ ለያዘን፣

ከውጭ ተመሳጥሮ፣ለባዕዳን አድሮ፣

ባንድ እንዳንነሳ ድምፃችንን ጭምር አፍኖ ላሰረን፣

ይህን መሠል ሰይጣን ገትሮ ለማቆም፣

የሳጥናኤል ተግባር፣ደግሞም እንዳይመጣ፣ነገ እንዳይደገም፣

ሴት ወንድም ይነሳ፣ሁሉም ህዝቤን ብሎ ፋኖ ሆኖ ይቁም!!

የዳያቢሎስ ጣጣ፣የዲያቢሎስ ተግባር፣እንጦሮንጦስ እንዲጣል፣

በቃኝ! ይብቃ ብሎ አሕዛብ ባንድ ይቁም!!

***ይህ ሰይጣን ይወጋ! መንፈሱም ይመታ***
***ሁሉም ይሰማራ በያለበት ቦታ፣***
***የርኩስ መንፈስ አርካሽ መድሃኒት ፍለጋ።***

የህዝቡን ህዝብነት፣ህዝብነቱን ጥሎ፣

ስብዕናን ጭምር፣ከአፈር ደባልቆ፣ከመሬት ቀላቅሎ፣

የታሪክን እንብርት እሱነቱን ገላጭ ሀገሩን ከፋፍሎ፣

ለቻይናው ላረቡ፣ለዶላር ከበርቴው ይኸው ግዙ ብሎ!!

ይሄው እርኩስ፣መንፈስ ከባንዶች ተጋብቶ፣

ለሆድ ካደሩ ጋር ሁሉን ተቀራምቶ፣

ፍሪዳ እየጣለ ውስኪ እየተራጨ፣

እስከመቼ ይኑር፣በሚኒሊክ ጊቢ እሱ እየፈነጨ??

ሣል ሣል ይደረግ የደነዘው ካራ፣

ነቃ ተጋ ይበል፣ተኝቶም ከሆነ የያዝነው ህሊና፣

ከዳዴ ተላቀን ራመድ ራመድ እንበል

አልመን እንምታ!አጥፊን አደባይተን---ገዳይን እንግደል!!

ይህን እርኩስ መንፈስ!

ጭንቅላቱን በለው፣ጉሮሮውን በጥስ፣

ለሚገል ሰይጣን ደጋግመህ አትሙት፣ገለኸው ተባረክ!ገለኸው ተቀደስ!

*ህዝብ ሁሉ ባንድ ይቁም፣*

*ይህ መንፈስ ይመታ፣ይህ እርኩስ ይወገር፣*

*ሁሉም ይሰማራ በያለበት ቦታ፣*

*የርኩስ መንፈስ አርካሽ መድሃኒት ፍለጋ።*

በሽታ አገር ወርሶ፣ዝሙትና ዕፁም ተከላካይ አጥቶ፣

ወግና ባህልም በወያኔ ሤራ ቅጥ አንባሩ ጠፍቶ፣

ያ ባለታሪክ ህዝብ !!

ዕድሜ ለማራዝም ፣አቃስቶ ለመሞት፣በአግባብ ለመቀበር ዕድሉንም አጥቶ

በብዛት ረገፈ እርኩስ መንፈስ መትቶት።

ላቅመ ሄዋን ስትደርስ፣ህይወት አስገድዷት ሴት እህት ስትሸጥ፣

ወጣቱ ተሰዶ በሺዎች ሲታሰር፣

አይኑ ተሸብቦ፣አፉ ተለጉሞ፣በየአረቡ አገር በዱላ ሲወገር፣

ከዚህ የተረፈው በውሃ ሲወሰድ፣ከባህር ሲቀበር፣

ይሄ እርኩስ መንፈስ ያደረሰው በደል ያስከተለው መዘዝ፣

እጅግ በጣም በዛ፣የትኛው ተጥሎ የትኛው ይነገር ??

*ህዝብ ሁሉ ባንድ ይቁም፣*

*ይህ መንፈስ ይመታ፣ይህ እርኩስ ይወገር፣*

*ሁሉም ይሰማራ በያለበት ቦታ፣*

*የርኩስ መንፈስ አርካሽ መድሃኒት ፍለጋ።*

እናት ሥታለቅስ ሀዘን ተድራርቦ፣ማድያት ተላብሳ፣

መሬት ተሸጦበት፣መሬት ያጣው አባት፣መሬት ላይ ተነጥፎ ሀዘንን ሲያገሳ፣

ይሄ ሁሉ በደል እየተፈፀመ፣እንዴት ይቻለናል ሕይወት አለን ማለት?

እንዴትስ ያቅታል ኃይልን አስተባብሮ ይህንን መመከት?

**ይቻላል፣በርግጥም ይቻላል ምንም አያዳግት፣!!**

**<u>ጥንቃቄ የሚያሻው፡-</u>**

**ይሄ እርኩስ መንፈስ፣ነጥሎ፣ነጣጥሎ፣ነጥሎ፣እንዳይጥልህ፣**

**በተነጠልክበት በህዝብ አስተፍቶ ነጥሎ እንዳይገልህ፣**

**በህዝብ ባገር ብሶት ውርድትን አልብሶ አንተን እንዳይቀብርህ፣**

**ዕርኩስን የሚያርቅ፣ከአሳይመሲህ ሁሎ አንተን የሚጠብቅ**

**እውነተኛ እምነት ባንገትህ አጥልቀህ ከልብህ አጠብቀህ**

**ረድፍህን አስተካክል ሕዝብ አገሬን ብለህ።**